# መመሪያ ቁጥር 218/2013

## የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የገንዘብ አጠቃቀም የሚመራበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ

የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ በኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሚቀመጠው ገንዘብ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እና አክሲዮናቸው ሙሉ በሙሉ በመንግስት የተያዘ አክሲዮን ማህበራትን እንዲሁም ከፈንዱ ላይ የሚደረገውን የክፍያ መጠን የመወሰን ሥልጣን ለገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሰጠ በመሆኑ፣

ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ የሚቀርብበትን እንዲሁም የፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም የሚመራበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 730/2004 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል::

## 1. አጭር ርዕስ

□ህ መመሪያ «የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የገንዘብ አጠቃቀም የሚመራበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁዓር 218/2013» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም:-

1. «የመንግሥት የልማት ድርጅት» ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 አንቀጽ 2 /1/ የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ የመንግስት የልማት ድርጅት እና አክሲዮኖቹ ሙሉ በሙሉ በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ አክሲዮን ማህበር ሲሆን፣ የመንግሥት የፋይናንስ ድርጅትን አይጨምርም።

2. "ፈንድ" ማለት በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ የተቋቋመው የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ነው።

3. "አዋጅ" ማለት የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 730/2004 ነው።

4. "ኤጀንሲ" ማለት የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ነው።

5. "ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን" ማለት የመንግሥትን የባለቤትነት መብት ለማስከበር ሲባል የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚሰይመው አካል ነው።

6. "ሚኒስቴር" ወይም" ሚኒስትር" ማለት እንደአግባብነቱ የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን መወሰን፣ የፈንዱ ተጠቃሚዎች ጥያቄያቸውን

የሚያቀርቡበትን እና ጥያቄው የሚመረመርበትን ሥርዓት መዘርጋት እና የፈንዱን ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት መወሰን ይሆናል፡፡

## 4. የፈንዱ የገንዘብ ምንጭ

ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኘው ገቢ ወደ ፈንዱ የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በየበጀት ዓመቱ ከሚያገኙት ትርፍ ላይ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ትርፍ፣
2. ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ የሚገኘው ገቢ፣
3. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከፈንዱ በብድር የወሰዱትና በብድር ስምምነቱ መሠረት ተመላሽ የሚደረግ ገንዘብ ፣
4. መንግሥት በተለየ ሁኔታ የሚወስነው ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚገኝ ገቢ፣

## 5. የፈንዱ የባንክ ሂሳብ

1. ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ እንዲሁም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ትርፍ የሚገኘው ገቢ ተቀማጭ የሚደረግባቸው ሁለት የባንክ ሂሳቦች ይኖራሉ፡፡
2. ሚኒስቴሩ የፈንዱን የባንክ ሂሳቦች ያስተዳድራል፡፡ ሲፈቀድም በፈንዱ የባንክ ሂሳቦች ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

## 6. <u>ጥያቄ አቀራረብ</u>

ከፈንዱ ገንዘብ እንዲመደብላቸው የሚፈልጉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የሆነውን ቅጽ በመሙላት ጥያቄያቸውን በሚከተለው አኳኋን ማቅረብ አለባቸው፡፡

1. ተጠሪነታቸው ለፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የሆነ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለአዳዲስ ኢንቬስትመንት፣ ለማሻሻያ ወይም ለማስፋፊያ ወይም ከደረሰባቸው ኪሣራ ለመውጣት የሚያስፈልገው ገንዘብ ከፈንዱ እንዲመደብላቸው በሚፈልጉበት ጊዜ የሚሰጣቸው ገንዘብ የሚውልበትን ተግባር አዋጭነት ከሚያሳይ ዝርዝር ጥናት ጋር ለኤጀንሲው ያቀርባሉ፡፡

2. ኤጀንሲው የቀረበውን የአዋጭነት ጥናት በመመርመር ጥያቄው ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው ከበኩሉ አስተያየት ጋር ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

3. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው ገንዘቡ ከፈንዱ እንዲመደብ ጥያቄውን ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

4. ተጠሪነታቸው ለሌላ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የሆነ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተመሳሳይ ከፈንዱ እንዲመደብላቸው የሚጠይቁት ገንዘብ የሚውልበትን ተግባር አዋጭነት ከሚያሳይ ዝርዝር ጥናት ጋር ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ያቀርባሉ፡፡ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ጥያቄው ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው ገንዘቡ ከፈንዱ እንዲመደብ ጥያቄውን ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

5. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የተፈቀደ ካፒታል ከፈንዱ እንዲከፈል የሚቀርብ ጥያቄ ካፒታሉ እንዲከፈል ማድረግ ካስፈለገበት ምክንያት ጋር እንደአግባብነቱ በኤጀንሲው ወይም በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ተደግፎ መቅረብ አለበት፡፡

6. ከዚህ ቀደም ከፈንዱ ገንዘብ በድጋፍ ወይም በብድር እንዲወስዱ ተፈቅዶ የተፈቀደውን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ያልተጠቀሙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጥያቄያቸውን በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አማካኝነት ሲያቀርቡ ቀሪው ገንዘብ ይከፈላል፡፡

## 7. የገንዘብ አፈቃቀድ

1. ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከፈንዱ የሚሰጠው ገንዘብ እንደሁኔታው በብድር፣ በድጋፍ ወይም በካፒታል መዋጮ መልክ ሊሆን ይችላል፡፡

2. ሚኒስቴሩ እንደአግባብነቱ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም በሌላ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ተደግፈው ከፈንዱ ገንዘብ ለመጠቀም የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ከአምስቱ ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንፃር በመመርመር ቅደም ተከተል ያወጣል፣ ገንዘቡ የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናል፡፡

3. ከፈንዱ ገንዘብ ወጪ ሊሆን የሚችለው የሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በሚኒስትሩ ታይቶ ሲፈቀድ ብቻ ይሆናል፡፡

4. ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከፈንዱ የሚፈቀደው ገንዘብ በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ስም ወደሚከፈት የባንክ ሂሳብ ገቢ ተደርጎ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

## 8. የተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን፡-

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሠረት ወደ ፈንዱ ገቢ ሊሆን የሚገባው ገንዘብ በወቅቱ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፣

2. ከፈንዱ ገንዘብ የተፈቀደላቸው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የወሰዱትን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ ማዋላቸውን ይከታተላል።

3. ከፈንዱ ገንዘብ በብድር የወሰዱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በብድር የወሰዱትን ገንዘብ በብድር ስምምነቱ መሠረት ተመላሽ ማድረጋቸውን ይከታተላል። ስለ ፕሮጀክቱ አፈፃፀምና ስለገንዘብ አጠቃቀም በየስድስት ወሩ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል።

## 9. ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 15 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሚያዝያ 3 ቀን 2004 ዓ.ም**

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር

# አባሪ

## ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ገንዘብ መጠየቂያ ቅጽ

1. ጠያቂው የመንግሥት የልማት ድርጅት ስም ______________________
______________________________________________________________

2. የተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ስም ____________________________________

3. የተጠየቀው ገንዘብ የሚውልበት ዓላማ

   ☐ ለአዲስ ኢንቬስትመንት ☐ ለማሻሻያ

   ☐ ለማስፋፊያ ☐ ከኪሣራ ለመውጣት

4. ፕሮጀክቱ ከአምስቱ ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ያለው ተያያዥነት ይብራራ፡፡

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

5. የአዋጭነት ጥናት ☐ ተያይዟል፡፡

6. የተጠየቀው ገንዘብ መጠን

   ______________________________________________________________

7. ገንዘቡ የተጠየቀው፣

   ☐ በድጋፍ ☐ በብድር

8. በብድር ከሆነ ተመልሶ የሚከፈልበት ጊዜ

   ______________________________________________________________

9. ገንዘቡ ከ ____________ ጊዜ ጀምሮ ጥቅም ላይ መዋል ይጀምራል፡፡
በ ______________ ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

10. የተቆጣጣሪ ባለሥልጣን አስተያየት _______________________
__________________________________________________________

የተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ፊርማ